


# ክርስቲያን እንዲዋሽ ተፈቅዶለታል?

13-2

## ውሸተኞች ምን ይመስላሉ?

1. ንግግራቸው ጥበብ የሞላበት የተንኮል ቃል ነው። ንግግራቸውና ተግባራቸው ፍጹም አይገናኝም። የሚናገሩት በጎ ሲመስል የሚኖሩት ግን ተንኮል የሞላበት ነው። “በአንደበቱ ሽንግሎአልና ኃጢአቱ ባገኘችው ጊዜ ይጠላታል። የአፉ ቃል ግፍና ሽንገላ ነው፤ ማስተዋልን፣ በጎ ማድረግንም ተወ፤ በመኝታው ጠማማነትን አሰበ፤ መልካም ባልሆነች መንገድ ቆሞአል፤ ክፋትን አይንቃትም” (መዝ. 36፥2-4)።

2. ምክራቸው በተንኮል የተሞላ ነው። “የኃጥአን ምክር ተንኮል ነው” (ምሳ. 12፥5)። ስለሌላው በጎ ሃሳብ ያላቸው ይመስላሉ፤ ከውስጣቸው ግን የተደበቀ መርዝ አለባቸው። በውሸተኞች ምክር ተመርተው ትዳራቸው የፈረሰ፣ ወዳጆቻቸውን ያጡ ሰዎች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም።

3. ፍቅራቸው እውነትነት የለውም። ወዳጄ መስለው ይቀርባሉ፤ ከውስጣቸው ግን መርዝን ይረጫሉ። ቅናትና ምቀኝነት በውስጣቸ የሞላ በመሆኑ ላይ ልዩን ፈገግታ ያሳዩ እንጂ ከውስጣቸ እውነትነት የለባቸውም። “የወዳጅ ማቁሰል የታመነ ነው፤ የጠላት መሳም ግን የበዝ ነው” (ምሳ. 27፥6)።

4. ብልጽግናቸው በኃጢአት የተገኘ ነው። ውሸት የሞላበትንና የተምታታ ሕይወታቸውን በማስተካከል ፈንታ እንደ ብልሃተኛና ታታሪ ሰው አድርገው ራሳቸውን ይቆጥራሉ። ሀብታቸው የተጠራቀመው በእውነት ላይ ትመሥርቶ አይደለም። “ቀፎ ወፎችን እንደሚሞላ እንዲሁ ቤታቸው ሽንገላን ሞታለች። እንዲሁም ከብረዋል፤ ባለጠጎችም ሆነዋል” (ኤር. 5፥27)።

## ውሸትን እንድናስወግድ ታዘናል

1. “የእውነት ከንፈር ለዘላለም ትቆማለች፤ ውሸተኛ ምላስ ግን ለቅጽበት ነው” (ምሳሌ 12፥19)።
2. “እያንዳንዳችሁ ከባልንጀራችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ” (ዘካር. 8፥16)።
3. “ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ” (ኤፌ. 4፥25)።

## ለምን እንዋሻለን?

ክርስቲያን ከቃሉ በራቀ ቁጥር የመንፈሳዊ ሕይወቱም በዚያው መጠን እየደረቀ ይሄዳል። ኃጢአትንም መለማመድ ይጀምራል። ኃጢአትን ቀስ በቀስ እየተለማመደ ሲሄድ፥ ጽድቅ እንደሠራ ይሰማዋል። ታድያ የዘመኑ ክርስትያኖች ሳይጨነቁ እንደ ልባቸው የሚዋሹት ኃጢአት አይደለም ብለው ይሆን?

1. መዋሸት ልማድ ሆኖብናል
የጥንት ክርስትያኖች እውነትን ብቻ በመናገራቸው ታሥረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ተሰቅለዋል። ከሞት ለማምለጥ መዋሸት ሲችሉ "እምቢ፤ ውሸትን አንናገርም" በማለት ሕውየታቸውን አጥተዋል። የዘመኑ ክርስትያኖች ግን ሰይፍ ሳይመዘዝብን፣ በሞት ሳይስፈራሩን ምላሳችን ውሸት ወደ መናገሩ ያዘነበለ በመሆኑ በቀላሉ እንዋሻለን። ምአዋሸትን በጣም በሕይውታችን ስለተለማመድነው አሁንማ እንደ ኃጢአት አይሰማንም። "ሐሰትን መናገርንም ምላሳቸው ተሞሮአል" (ኤር. 9፥5)። ዋሽተን ካገኘነው ገንዘብ አሥራት በመክፈል ቅድስናን ለመግዛት ሳናውቀው ሞክረናል። ይሁን እንጂ ዋሽተን ያመጣነው ገንዘብ እንግዚአብሔርን ከማስደሰቱ ይልቅ ልቡን ይሰብረዋል።

2. ውሸት ኃጢአት አይመስለንም
የውሸታሞች ዕድልና ፋንታ ምን እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ሥፍራ ብናነብም፥ መዋሸት እንደ መስረቅና እንደ መግደል ኃጢአት መሆኑን የተረዳን አይመስለኝም። ኃጢአት ስለማይመስለንም ህሊናችን ሳይጨንቅብንና ሳንፈራ ተዝናንተን እንዋሻለን።

3. ራሳችንን ለመሸፈን ስንል እንዋሻለን
ሰው ራሱን ይወዳል። ስለሆነም ሌላ ሰው ድካሙን እንዲያውቅበት አይፈልግም። ራሱን ገላልጦ ቢያሳይ ከሌላው ሰው የሚፈልገውን መከበርን ያጣል። ስለዚህ ያልሆነው እንደሆነ፣ ያልያዘውን እንደያዘ፣ ያልተማረውን እንደ ተማረ አድርጎ ያቀርባል። እንደ አቅሙ ቢኖር መከበርን ያሳጣኛል ስለሚል፣ የሚያስከብረውን ሀብት በአጭሩ ለማግኘት የውሸት ጎዳና ይቀይሳል። በደሞዙ መኖር የሚያሳንሰው መስሎ ከተሰማው ባቋራጭ የሚበለጽግበትን የውሸት ዘዴ ይጠቀማል።

4. የሚያደርሰውን ጉዳት ባለማወቅ
ክርስትያን ኃጢአትን እያወቀ አይለማመድም። ኃጢአትን አይለማመድም አልን እንጂ ኃጢአትን አይሠራም አላልንም። መለማመድ ስንል ደጋግሞ ያንኑ ኃጢአት መሥራት ማለታችን ነው። ኃጢአት ሞትን እንደሚያስከትል ክርስትያን ስለሚያውቅ፥ ኃጢአት ሲሠራ ደስ አይለውም። ውሸት ኃጢአት እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። ኃጢአት ከሆነ ደግሞ የግድ መቀጣት አለበት። ይህን ካልተገነዘብን፥ በኃጢአት ውስጥ ለመኖር ለራሳችን ነጻነት እንሰጠዋለን። በኃጢአት ከኖርን ደግሞ ጌታን በቅጡ አላወቅነውም ማለት ነው። ሃናንያና ሰጲራ የእግዚአብሔርን መንፈስ ለመዋሸት በመሞከራቸው ፍርድ በላያቸው ላይ አስከተሉ። ዛሬስ እንደ ሃናንያና እንደ ሰጲራ አንዴ ብቻ ሳይሆን፥ ደጋግመው የሚዋሹ ክርስትያኖች መንፈሳዊ ዕድገታቸው ምን ያህል ነው? የጥንት መነፈሳዊ አባቶች ውሸትን ከአደጋ ማምለጫ መሰላል አድርገው በመጠቀማቸው ዋጋቸውን በልጆቻቸውና በልጅ ልጆቻቸው በኩል አግኝተዋል። እኛስ በመዋሸት የተሞላው ሕይወታችን ሳይቀጣ ያልፍ ይሆን?

**"ውሸተኛ ከንፈር ከእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው፤ እውነትን የሚያደርጉ ግን በእርሱ ዘንድ የተወደዱ ናቸው"**
ምሳሌ 12፥22

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**